# የወላጅ መመሪያ
# ለልጅዎ ቀዶ ጥገና/ሕክምና መዘጋጀት
# A Parent's Guide
# Preparing for Your Child's Surgery/Procedure (Amharic)

**ወደ Swedish** የሕክምና ማዕከል እንኳን ደህና መጡ። ለእርሶ እና ለልጅዎ የላቀ ሕክምና ለማቅረብ በጉጉት እንጠባበቃለን። ግባችን በማንኛውም አኳያ በ Swedish የሚኖርዎት ገጠመኝ በሙሉ እጅግ ጥሩ መሆኑን ለማየት ነው።

## የቀዶ ጥገናዎ/ሕክምናዎ ቀጠሮ የተያዘልዎት፥

| | | |
|---|---|---|
| ☐ | BALLARD ካምፓስ | 206-781-6245 |
| ☐ | ቼሪ ሂል ካምፓስ (Cherry Hill campus) | 206-215-3200 |
| ☐ | ፈርስት ሂል ካምፓስ (First Hill campus) | 206-215-3200 |
| ☐ | ኦርቶፔዲክ ኢንስቲትዩት (Orthopedic Institute) | 206-215-3200 |
| ☐ | ኢሳኳ ካምፓስ (Issaquah campus) | 425-313-5330 |

*ለሁሉም ካምፓስ የነፃ ስልክ መሥመር 1-866-851-5111*

## ለልጅዎ ቀዶ ጥገና/ሕክምና ለመዘጋጀት የሚቀጥሉትን ቅደም ተከተሎች እባክዎ ይከተሉ፥

1. ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ለስዊድሽ ሜዲካል ማዕከል ይደውሉ፥
   - ለልጅዎ ቀጠሮ ለመያዝ በሆስፒታሉ ለመመዝገብ
   - **ለአስፈላጊ** የቅድመ መግቢያ የስልክ ቀጠሮ ለመያዝ። ለመመዝገብ እና ቀጠሮ ለመያዝ 15 ደቂቃ ይጠብቁ። የልጅዎ ኢንሹራንስ ካርድ መያዝ አለብዎት።
2. ከስዊድሽ የስልክ መልእክት ከደረሰዎት፣ በመልእክቱ ላይ በተሰጠው ስልክ ቁጥር መልሰው ይደውሉ።
3. አንዴ ለልጅዎ ሕክምና በሆስፒታሉ ቀጠሮ ከተያዘ በኋላ፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎ ፈቃድ እንደሰጠ ለማረጋገጥ ስልክ ይደውሉ።
4. ይህንን መግለጫ ጽሁፍ በጥንቃቄ ያንብቡ እንዲሁም ለቅድመ ቀዶ ጥገና አመጋገብ እና የመድሐኒት አወሳሰድ መመሪያዎች የተለየ ትኩረት ያድርጉ።

## ጠቃሚ የገንዘብ ነክ (ፋይናንስ) መረጃ

የሚከተሉትን ለማረጋገጥ የእርስዎን ኢንሹራንስ ኩባንያ ማነጋገር ኃላፊነትዎ ነው፥

- ለባለሙያ ክፍያ እና ለሆስፒታሉ ክፍያ ዶክተርዎ ፈቃድ ለማግኘታቸው
- ለልጅዎ የሚደረገውን የክፍያ ሽፋን ገደብ እና የማይሸፈነው ወጪ ከግል ገንዘብዎ እንደሚከፈል ማወቅዎን

ለቀዶ ጥገናው ስለሚወጣው ወጪ ወይም ክፍያ ለሚኖሩ ጥያቄዎች በ 206-320-5300 መልስ ሊያገኙ ይችላሉ።

## ከቅድመ መግቢያ ክሊኒክ ጋር የሚያደርጉት የስልክ ቀጠሮ

**(እስከ 30 ደቂቃ ድረስ ይጠብቁ)**

ቀን፥ ____________ ሰዓት፥ ____________

ለቀጠሮዎ ከርስዎ ጋር የሚይዙት፥

- የልጅዎን ወቅታዊ የመድሐኒቶች ዝርዝር
- የቤተሰብዎ ዶክተር ስምና የስልክ ቁጥር
- የልጅዎ ያለፈ ግዜ የቀዶ ጥገናዎች፣ ወቅታዊ የጤና ችግሮች እና ማንኛውም የልብ ምርመራ ሪፖርት ዝርዝር

## ለልጅዎ ቀዶ ጥገና /ሕክምና መቼ እንደሚደርሱ

ቀን፥ ____________ ሰዓት፥ ____________

## የቅድመ ቀዶ ጥገና አመጋገብ መመሪያዎች፥

ልጁ የሚታኘክ ምግብ ለመጨረሻ ጊዜ የሚመገበው፥ ____________

ልጁ ለመጨረሻ ጊዜ ፎርሙላ ወይም ያልተጣሩ ፈሳሽ ነገሮችን መጠጣት የሚችለው፥ ____________

ልጁ የጡት ወተት ለመጨረሻ ጊዜ መጠጣት የሚችልበት፥ ____________

ልጁ የተጣራ ፈሳሽ መጠጣት የሚችልበት የመጨረሻ ጊዜ፥ ____________

*በዚህ መጽሔት ውስጥ ለእያንዳንዱ ካምፓስ የካርታ አቅጣጫና መኪና ማቆሚያ መመሪያዎች ይገኛሉ። በካርታው ላይ የቅድመ መግቢያ እና የቀዶ ጥገና/የሕክምና መመዝገቢያ ቦታዎች በዝርዝር ተጽፈዋል።*

***ለበለጠ መረጃ በ "Health & Patient Services > Patient & Visitor Information" ስር www.swedish.org የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።***

*ስለ ታካሚዎች መብትና ኃላፊነት መረጃ ለማግኘት www.swedish.org/patients-rights-responsibilities የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።*

SWEDISH
PEDIATRICS
Extraordinary care. Extraordinary caring.℠

# ቀዶ ጥገና ወይም ሕክምና እና ልጅዎ

በስዊድሽ የቀዶ ጥገና ሕክምና ለልጆች አሳፋሪ ሊሆን እንደሚችል እንገነዘባለን። በዚህ ምክንያት ነው መላው የሕክምና ክንውን በተቻለ መጠን በመልካም ሁኔታ እንዲፈፀም የምንጥረው። ልጅዎ እጅግ በጣም ዘመናዊ በሆነ የሕክምና ቴክኖሎጂ በመጠቀም በጣም ከፍተኛ ሥልጠና በወሰዱ ባለሙያዎች እየተረዳ—ለልጅዎ ተስማሚ በሆነ አካባቢ ሁሉ ሕክምና እንደሚሰጠው እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ይህንን ጽሁፍ በጥሞና በማንበብ እና የተሰጠውን መመሪያ በመከተል ለልጅዎ ሕክምና ዝግጅት ሊረዱ ይችላሉ።**

- የሆስፒታሉ ቆይታ ልምዱ በቅድመ ምዝገባ ቀጠሮ ይጀመራል። ለዚህ **አስፈላጊ** የስልክ ቃለ መጠይቅ ቀጠሮ ለመያዝ እባክዎን ለሆስፒታሉ ይደውሉ። በዚህ የስልክ ጥሪ ወቅት አንድ ነርስ የልጅዎን የሆስፒታል ቻርት ለመሙላት ጥያቄ ይጠይቁዎታል፣ ምን ሊሆን እንደሚችልም ማብራሪያ ይሰጡዎታል እንዲሁም ለማንኛውንም ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ። ለቃለ መጠየቁ ሲቀርቡ እባክዎን የልጅዎን መድሐኒት ይዘው ይምጡ።
- የቀዶ ጥገና ሕክምናው በሚድረግበት ቀን፣ ሆስፒታሉን ጠንቅቆ ማወቁ የልጅዎ እና የእርሰዎን ጭንቀት የበለጠ ሊያቃልል ይችላል። የቀዶ ጥገና ሕክምና እና የህፃናት የሕክምና ክፍልን ከሰኞ እስከ ዓርብ መጎብኘት ይችላል። ቀጠሮ ለመያዝ ከፈለጉ በ 206-386-6283 ለልጅ ህይወት ልዩ ሐኪም ይደውሉ።
- የልጅዎ ቀዶ ጥገና ሕክምና በሚካሄድበት ዕለት ከአንስቲስዩሎጂስቱ ጋር እንዲገናኙ ይደረግና ፈቃደኛ መሆንዎን የሚገልፁበት ቅጽ ላይ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። **ከ 18 ዓመት በታች ለሆኑ ለማንኛውም ታካሚ የቀዶ ጥገና ሕክምናው በሚፈፀምበት ዕለት ወላጅ ወይም ሕጋዊ ሞግዚት ወይም አሳዳጊ መገኘት አለበት።** ጊዜያዊ ጠባቂ ወይም ሞግዚት ከሆነ የህጋዊ ሞግዚትነት ወይም ጠባቂነት ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል።
- ሕክምና በመከታተል ባለው ልጅዎ ላይ የበለጠ ትኩረት እንዲያደርጉለት ለሌሎች ልጆችዎ ጠባቂ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ እንመክርዎታለን። **ቀዶ ጥገና ሕክምና በሚደረግበት አካባቢ ወይም በቀዶ ጥገና ክፍሎች ውስጥ ወንድምና እህት እንዲገቡ አይፈቀድም።** በቀዶ ጥገና ሕክምና ሒደት ወቅት ብዙ ወላጆች በተቻለ መጠን ከልጆቻቸው ጋር አብሮ መሆን ይፈልጋሉ፣ ይህን ሁኔታ በሚገባ እንረዳዋለን። ነገር ግን ልጅዎ ወደ ቀዶ ጥገና ሕክምናው ክፍል የማደንዘዣ መድሐኒት (አንስትዥያ) ለመውሰድ ሲገባ እና ልጁን ከሰመመን በሚነቃበት ወቅት አንድ ወላጅ ብቻ ሊገኝ ይችላል። በዚህ መንገድ የሁሉንም ሰው ደህንነት እና ምቾት ልንጠብቅ እንችላለን። ልጅዎን ወደ ቤት ለመወሰድ ሲዘጋጁ ሁለቱም ወላጆች ሊገኙ ይችላሉ።

**የልጅ ህይወት ልዩ ሐኪሞች (እስፔሻሊስቶች)**

የልጅ ህይወት ልዩ ሐኪሞች የጤና እንክብካቤ የሚያደርገው ቡድን አንዱ አካል ናቸው። ሥራቸው ለቀዶ ጥገናው ወይም ለሕክምናው ከእድሜ ጋር የተመጣጠነ ዝግጅት ሲደረግ ማገዝ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ከልጅዎ ጋር እንዴት እንደሚነጋገሩ ለማወቅ ጥያቄ ካለዎት እባክዎን 206-386-6283 ይደውሉ።





# የቅድመ ቀዶ ጥገና መድሐኒት መመሪያዎች፡-

ልጅዎ ደምን የሚያቀጥን መድሐኒት ወይም ማንኛውንም አስፒሪን በውስጡ የያዘ ምርት የሚወስድ ከሆነ እባክዎን የቀዶ ጥገና ሕክምና ባለሙያውን ያነጋግሩ። የቀዶ ጥገና ሕክምናው ከመከናወኑ በፊት መድሐኒቱን ማቆም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

*በዶክተሩ፣ በቀዶ ጥገና ሐኪሙ ወይም በአንስትስዩሎጂስቱ ካልታዘዘ በስተቀር የቀዶ ጥገና ሕክምናው ከመካሄዱ በፊት መድሐኒቱን እንዴት እንደሚወስድ እባክዎን ከዚህ በታች ያለውን መመሪያ ልጅዎ እንዲከተል ያድርጉ።*

### ከቀዶ ጥገናው/ሕክምናው ሁለት ሳምንት ቀደም ብሎ፥

ለምግብነት የሚገለግሉ ተጨማሪ ቫይታሚኖችን በሙሉ መውሰድ ያቁሙ።

### ከቀዶ ጥገናው ሦስት ቀናት ቀደም ብሎ፥

እንደ Advil፣ Aleve፣ DayPro፣ Feldene፣ Ibuprofen፣ Indocin፣ Lodine፣ Motrin፣ Naproxen፣ Naprosyn እና Voltaren የመሳሰሉትን ስቴሮይድ የሌለባቸውን፣ የግለት ማብረጃ (anti-inflammatory) መድሐኒቶችን ሁሉ መውሰዱን ያቁሙ።

### ልጅዎ የቀዶ ጥገና በሚያደርግበት ቀን ጠዋት፥

ልጅዎ ጠዋት ጠዋት እንዲወስድ የታዘዙለትን ሌሎች የተለመዱ መድሐኒቶችን በሙሉ በጥቂት ውሃ መዋጡን ያረጋግጡ። ልጅዎ የአስም መድሐኒት የሚወስድ ከሆነ እንዲጠቀም እና ወደ ሆስፒታል ይዞ እንደሚጣ ያድርጉ።

# ጠቃሚ መመሪያዎች

### ከቀዶ ጥገናው በፊት ያለው ቀን፥

- ☐ በጤንነቱ ላይ ልጅዎ ማንኛውንም ለውጥ ካመጣ ለዶክተሩ ይደውሉ፣ ልጅዎ ጉንፋን ከያዘው፣ ሳል፣ ትኩሳት፣ የፊኛ ሕመም፣ የቆዳ መቆጣት፣ ተቅማጥ ወይም ሌላ ኢንፌክሽን ካለው ለዶክተሩ ይደውሉ።
- ☐ በዚህ መጽሔት ገጽ አራት ላይ ያለውን የቅድመ ቀዶ ጥገና አመጋገብ መመሪያ አንብበው ይከተሉ።

### የቀዶ ጥገናው ቀን፥

- ☐ ወደ ሆስፒታል ከመምጣትዎ በፊት ልጅዎን ገላውን እና ፀጉሩን ይጠቡት። ፀጉሩን ካጠቡት በኋላ ምንም ዓይነት የፀጉር ቅባት አይቀቡት። ይህን ቀደም ባለው ምሽት ላይ ማድረግ ይችላል።
- ☐ ልጅዎ ምንም ዓይነት ሜክ አፕ ወይም የግል መኳኳያዎችን፣ እንደ ሄርስፕሬይ፣ ሽቶ፣ ጄል፣ አፍተርሼብ፣ የፊት ቅባት፣ የዘይት ቅባት፣ ሎሽን ወይም ሄርኮንዲሽነር የመሰሉትን እንዲጠቀም አያድርጉ። ሳሙና እና ሻምፑ ብቻ ይጠቀሙ።
- ☐ ልጅዎ ሰፊ፣ እና ምቾት ያለው ልብስ እንዲለብስ ያድርጉ።
- ☐ ሁሉንም የልጅዎን ጌጣጌጦች አውልቀው ቤት ያስቀምጡ (ሁል ጊዜ የሚያደርገውንም ጨምሮ)።
- ☐ ልጅዎ የቅድመ ቀዶ ጥገና አመጋገብ መመሪያዎችን መከተሉን ያረጋግጡ **(ገጽ 4 ላይ ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)። መመሪያዎቹን ካልተከተለ ቀዶ ጥገናው ሊዘገይ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።**
- ☐ ሆስፒታል በሰዓቱ መገኘት አለበት።
- ☐ መኪና ለማቆሚያ ጊዜ ይኑርዎት (መጽሔቱ ላይ ያለውን ካርታ ይመልከቱ)።
- ☐ ልጆዎ ለአስማ የሚረዳ መተንፈሻ የሚጠቀም ከሆነ፣ እባክዎ ይዘው ይምጡ።
- ☐ አስፈላጊ ከሆነ፣ የልጁ ሞግዚት ወይም አሳዳጊ መሆንዎን የሚገልጽ ማስረጃ ይዘው ይምጡ።
- ☐ ልጅዎ የተለየ የአመጋገብ ፍላጎቶች ካሉት እባክዎን የሚመርጠውን የምግብ ዓይነት ይዘው ይምጡ።
- ☐ በስዊድሽ የመኪና ማቆሚያ ዋጋ ከቦታ ቦታ ሊለያይ ይችላል። ክፍያ ለመፈጸም ከፈለጉ እባክዎን ጥሬ ገንዘብ፣ ዴቢት ወይም ክሬዲት ካርድ ይዘው ይምጡ። ለመኪና ማቆሚያ ዋጋ ቅናሽ አይፈቀድም።

**አስፈላጊ**

## የቅድመ ቀዶ ሕክምና አመጋገብ መመሪያዎች

| | |
|---|---|
| **8** ሆስፒታል ውስጥ ለሕክምና ከመግባትዎ በፊት ያሉ ሰዓቶች | **ልጅዎ** ማንኛውንም የሚታኘክ ምግብ መመገብ እንዲያቆም ያድርጉ። ፈሳሽ መወሰዱን ይቀጥል።<br><br>**ምንም** ምግብ<br>**ምንም** እንደ ከረሚላ የሚመጠጡ ነገሮችን<br>**ምንም** ማስቲካ |
| **6** ሆስፒታል ውስጥ ለሕክምና ከመግባትዎ በፊት ያሉ ሰዓቶች | **እንደ** ውሃ ያልጠራ ፈሳሽ ለልጅዎ መስጠትዎን ያቁሙ።<br><br>**ምንም** ዓይነት ወተት (ከጡት ወተት በስተቀር)፣ ያልተጣራ ጭማቂ፣ ወይም የዱቄት ወተት እንዳይሰጡ<br><br>**ምንም** ነገር ያልተጨመረበት የጡት ወተት እና የተጣራ ንፁህ ፈሳሽ ለልጅዎ መስጠትዎን ይቀጥሉ።<br><br>7-up፣ ጌትሬድ፣ ማጣፈጫ የሌለው ጄሎ፣ የተጣራ የአፕል ጭማቂ ለልጅዎ መስጠት ይችላሉ።<br><br>**ምንም** ወተት<br>**ምንም** የዱቄት ወተት<br>**ምንም** ያልተጣራ ጭማቂ<br>**ምንም** የፍራፍሬ ማር<br>**ምንም** የተደባለቀ ጭማቂ (ስሙዚ) |
| **4** ሆስፒታል ውስጥ ለሕክምና ከመግባትዎ በፊት ያሉ ሰዓቶች | **የጡት** ወተትመስጠት ያቁሙ |
| **2** ሆስፒታል ውስጥ ለሕክምና ከመግባትዎ በፊት ያሉ ሰዓቶች | **በዶክተሩ** የታዘዘ መድሐኒት ካልሆነ በስተቀር ለልጅዎ ምንም ነገር በአፍ መስጠት ያቁሙ።<br><br>**ምንም** ውሃ<br>**ምንም** ንፁህ ፈሳሽ |

**በልጅዎ ዶክተር፤ የቀዶ ጥገና ሐኪም ወይም አንስትስዮሎጂስት ካልታዘዘ በስተቀር፣ ልጅዎ የቀዶ ጥገና ሕክምና ከማድረጉ በፊት እነዚህን የአመጋገብ መመሪያዎች መከተል ይኖርበታል። መመሪያውን ካልተከተሉ ሕክምናው ወይም ቀዶ ጥገናው ሊዘገይ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።**

# የማገገሚያ ክፍል

የማገገሚያ ክፍል ውስጥ ልጅዎ በልዩ ሁኔታ በሰለጠኑ ነርሶች እንክብካቤና ተገቢውን ሕክምና ያገኛል። በማገገሚያው ክፍል ውስጥ ልጅዎ የሚቆይበት ጊዜ እንደሁኔታው ይለያያል። ልጅዎ እንዲያገግም የእርሶ ምቾት እና ድጋፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንረዳለን፣ ስለሆነም ልጅዎን በቶሎ እንዲያዩ የተቻለን ሁሉ እንደምናደርግ ልናረጋግጥልዎት እንወዳለን።

# በሆስፒታል ውስጥ መቆየት

ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ልጅዎ በሆስፒታሉ ውስጥ ተኝቶ እንዲታከም ከተደረገ፣ በቆይታው ወቅት አንድ አዋቂ ሰው ሌሊት ከልጁ ጋር እንዲቆይ እንመክራለን። ያጋጣሚ ሆኖ፣ ስዊድሽ በአሁኑ ወቅት ታካሚ ላልሆኑ ማናቸውም ልጆች የልጆች እንክብካቤ (ቻይልድኬር) አገልግሎት አይሰጥም።  ወንድምና እህቶች በሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ በሚታከመው ልጅ ክፍል ውስጥ ሌሊት ከርሱ ጋር እንዲቆዩ አይፈቀድም። ሕመምተኞች መጎብኛ ስዓት ከጥዋት 5 ሰዓት እስከ ምሽቱ 9 ስዓት ድረስ ነው። ወንድምና እህቶች ታካሚውን በእነዚህ ስዓት ሊጎበኙ ይችላሉ፤ ከ 12 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ግን ከአዋቂ ሰው ጋር መሆን አለባቸው።

# ወደ ቤት ለመመለስ ማቀድ

ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ እቤትዎ ለልጅዎ እንክብካቤ እንደሚያደርጉ ለማወቅ የቀዶ ጥገና ሐኪሙን ቢሮ ይጠይቁ። ልጅዎ ወደ ቤቱ እንዲሄድ ቀጠሮ በተያዘለት ቀን (በቀዶ ጥገና ሕክምናው ዕለት ወይም ሕክምናውን ካጠናቀቀ በኋላ) እርስዎ ወይም ሌላ ፈቃድ የተሰጠው አዋቂ ሰው ልጁን ወደ ቤት እንዲወስድመገኘትአ **ለበት**። (በሕክምናው እለት ልጁን ወደ ቤት ይዞ የሚሄድ አዋቂ ሰው ከሌለ ሕክምናው ይሰረዛል።) ልጆች ብቻቸውን መኪና ነድተው ወይም በአውቶቢስ መሄድ **አይችሉም**። ከአዋቂ ሰው ጋር ሆነው በታክሲ መሄድ ይችላሉ። ሁሉም ታካሚዎች፣ በማንኛውም እድሜ ውስጥ የሚገኙት፣ ከቀዶ ጥገና ሕክምናው በኋላ ወይም በሆስፒታል ተኝተው ሲታከሙ ከቆዩ በኋላ በመጀመሪያው ምሽት ላይ እቤት ከነሱ ጋር አዋቂ ሰው ሊኖር ይገባል።

# የልጅ ህይወት ልዩ ሐኪሞች (እስፔሻሊስቶች)

በ Swedish፣ አንድ ልጅ በሆስፒታል ውስጥ ሲቆይ ፍርሃት እንደሚሰማው እና እንደሚደናገር እንረዳለን። ስለዚህም ነው፣ የልጅ ሕይወት ልዩ ሐኪሞች የህፃናት ጤና ጥበቃ ባለሙያዎች ቡድን አንድ አካል እንዲሆኑ ያደረግናቸውም በዚህ ምክንያት ነው። በ Swedish ያሉ የልጅ ሕይወት ልዩ ባለሙያዎች (እስፔሻሊስቶች) ልጆችና እና ቤተሰቦቻቸው በሆስፒታል ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ በስሜት እና በእድገት ጉዳይ የሚደርስባቸውን አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲቋቋሙ ከጎናቸው በመሆን እርዳታ ያደርጉላቸዋል።

የእያንዳንዱን ልጅ ቤተሰብ፣ ባህል እና የእድገት ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት የልጅ ሕይወት ስፔሻሊስቶች፥

- ልጆችን ለቀዶ ጥገና፣ ሕክምና፣ ምርመራ እና እንክብካቤ ለማዘጋጀት ለእድገታቸው ተገቢ የሆነ ጨዎታ እና ትምህርት ይጠቀማሉ።
- በሆስፒታል ጉብኝት በሚደረግበት ጊዜ የልጁን ስሜታዊ፤ ማህበራዊ እና የእድገት ለውጥ ለመደገፍ ጠንክረው ይሠራሉ።
- ልጆች ስለሆስፒታሉ ያላቸውን ፍርሀት እና ጥርጣሬ ለማስወገድ የቅድመ ሕክምና ትምህርት ወይም የሕክምና ጨዎታን እንደ መሣሪያ ይጠቀማሉ።
- ለልጆች እና ለቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ሰጪ፣ መልካም የሆኑ አስተምህሮ፣ እንዲሁም የጨዋታ፣ የቀልድ፣ የትምህርት እና ራስን የመግለፅ እድል እንዲኖራቸውም ያደርጋሉ።

## ልጅዎን ወደ ሆስፒታል ሄዶ እንዲጎበኝ ማዘጋጀት

ሆስፒታልን ሲጎበኙ ምን መጠበቅ እንዳለብዎት ማወቅ ብዙ የተለመዱ ፍረሐቶችን እና ጭንቀቶችን ለማስወገድ ሊረዳ ይችላል። በስዊድሽ የሕክምና ማዕከል ወስጥ በሚከናወን የቀዶ ሕክምና ሒደት ውስጥ ልጆችን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ በሚደረገው ጥረት፣ የሕፃን ህይወት ፕሮግራም ልጆቹን እና አስታማሚዎችን ቀጠሮ ለተያዘለት የቀዶ ጥገና ሕክምና ለማዘጋጀት የቅድመ ቀዶ ጥገና ሕክምና ጉብኝት ያደርጋል። እነዚህ ፕሮግረሞች አንድ-ለአንድ የሚካሄድ የሚካሄዱ የትምህርት ክፍሎች ሲሆኑ፣ በእድሜ ተገቢ የሆነ ትምህርትን እና የቅድመ ቀዶ ጥገና፣ የቀዶ ሕክምና እና የድህረ ቀዶ ጥገና/ ታካሚው ያለበትን የሆስፒታል አካባቢ መጎብኘትን ይጨምራል። በቀዶ ጥገና ሕክምናው ቀን ልጅዎ በሆስፒታሉ ውስጥ የሚያያቸውን ቦታዎች ማየትና የሚሰማቸውን ድምጾች መስማት ስለሆስፒታሉ እንዲያወቁ ሊያረጋግጥልዎት ይችላል። ጉብኝቶቹ አስደሳች፣ የእርስ በርስ ሲሆኑ የልጅዎን እና የቤተሰቡን ማህበራዊ እና ስሜታዊ ፍላጎት ባገናዘበ መልክ የተወጠኑ ናቸው።

***ጥያቄ ካለዎት ወይም የቅድመ ቀዶ ጥገና ሕክምና ጉብኝት ለማድረግ ከፈለጉ፣ እባክዎን ለልጅ ሕይወት ቡድን በ 206-386-6283 ይደውሉ።***



### ተልእኮ

የስዊድሽ የልጅ ህይወት ባለሙያዎች የህፃናትን፣ የልጆችን፣ የወጣቶችን እና የቤተሰቦቻቸውን እድገት፣ ጤንነትና ደህንነት የሚጎዱ አስጨናቂ ወይም አሰቃይ ገጠመኞችና ሁኔታዎችን ለመቀነስ ይጥራሉ። የልጅ ህይወት ልዩ ባለሙያዎች፣ በምዘና ጣልቃ በመግባት፣ በመከላከል፣ ጥብቅና በመቆም እና በትምህርት የህፃናትን፣ የልጆችን እና የወጣቶችን ጤናማ እድገት እና ለማጎልበት ጨዋታን እንደ መፈወሻ መሳሪያ ይቆጥሩታል።

# የአንስትኻያ (የማደንዘዣያ) ሕክምና

***ልጅዎ እንዳያውቅ እና ህመሙ እንዳይሰማው ስለሚደረግ አንስትኻያ (የማደንዘዣ መድሐኒት) የቀዶ ጥገና ሕክምና በሚከናወንበት ጊዜ አስፈላጊ ነው።***

## የህፃናት ሐኪም፣ አንስትሲዮሎጂስት ሚና ምንድነው?

አንስትሲዮሎጂስት ማለት በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ ሐኪም ሲሆን የቀዶ ጥገና ሐኪሙ ሕክምናውን በሚያካሂድበት ወቅት ለልጅዎ ሰላማዊና ደህንነቱ የተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርግ ባለሙያ ነው። አንስትሲዮሎጂስቱ ለልጅዎ የማደንዘዣ መድሐኒት ይሰጠውና የጤንነቱን ሁኔታ ያለማቋረጥ ይከታተላል። የአኒስቴቲክ (ማደንዘዣ) መድሐኒት 3 ደረጃዎችን ያካትታል፥ በእንቅልፍ መያዝ፣ እንቅልፉ መቆየት፣ እና ከእንቅልፍ መንቃት ናቸው።

## የልጁ አንስትሲዮሎጂስት የሚሆነው ማን ነው?

ልጅዎ በፔድሪያትሪክ አንስትሲዮሎጂ በሰለጠነ አንስትሲዮሎጂስት የማደንዘዣ መድሐኒት ይሰጠዋል። ለልጅዎ የማደንዘዣ መድሐኒት የሚሰጠው ሐኪም (አንስትሲዮሎጂስት) የሚመደበው የቀዶ ጥገና ሕክምና ከመደረጉ በፊት ባለው ምሽት ነው። የተለየ አንስትሲዮሎጂስት እንዲመደብሎት ለመጠየቅ በ 206-215-3656 ቁጥር ይደውሉ።

## አንስትሲዮሎጂስቱን መቼ አገኛለሁ?

የቀዶ ጥገና ሕክምናው በሚደረግበት ቀን ስለ ልጅዎ የሕክምና ታሪክ የሚጠየቅዎትን እና ስለማደንዘዣ መድሐኒቱ እቅድ የሚያነጋግሮትን አንስትሲዮሎጂስት ይገናኛሉ። ሆኖም ግን ቀደም ብለው በ 206-215-3656 ቁጥር በመደወል ከአንስትሲዮሎጂስቱ ጋር መነጋገር ይችላሉ።

ከዚያም ከአንስትሲዮሎጂስቱ መነጋገሮዎን እና ሁኔታውን መረዳትዎን እንዲሁም ልጅዎ የቀዶ ጥገና ሕክምና ሲደረግለት ማደንዘዣያ መድሐኒት እንዲወስድ መስማማትዎን በአንስትኻያ ልዩ የፈቃድ ቅጽ ላይ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ።

## የማደንዘዣ መድሐኒቱ የሚሰጠው እንዴት ነው?

የተለያዩ ቴክኒኮችን መጠቀም የሚቻል ሲሆን፣ መድሐኒቱን በደም ስር ውስጥ በመስጠት ወይም የማደንዘዣ መድሐኒቱ በመተንፈሻ ማስክ በመጠቀም ሊወሰድ ይቻላል። አንስትሲዮሎጂስቱ በልጁ እድሜ፣ ስብእና፣ በልጁ የማደንዘዣ መድሐኒት አወሳሰድ የበፊት ተሞክሮ እና ልዩ የሕክምና ሁኔታዎች መሠረት የልጅዎ ጥንቃቄ ደህና የሆነውን ቴክኒክ ይመርጥሎታል።

## ልጄ ቅድመ መድሐኒት ይደረግለታል?

አንስትሲዮሎጂስቱ ለልጅዎ ቅድመ መድሐኒት ሊሰጥ ይችላል (ከቀዶ ጥገና ሕክምና በፊት)። ነገር ግን ልጁ እንቅልፍ ሲይዘው የወላጁ ከአጠገቡ መገኘት የመድሐኒቱን ያህል ጠቃሚ ነው።

## ልጄ እንቅልፍ ሲይዘው ባጠገቡ መሆን እችላለሁ?

ከ 1 እስከ 8 ዓመት የደረሰ እድሜ ያላቸው ብዙ ልጆች አንዱ ወላጅ በተገኘበት የማደንዘዣ መድሐኒት መውሰድ ይችላሉ። ሆኖም ግን ለደህንነት ሲባል፣ ልጁ ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር ካለበት፣ ድንገተኛ የቀዶ ጥገና የሚደረግ ከሆነ ወይም ሕፃኑ ከ 1 ዓመት ያነሰ እድሜ ካለው ወላጆችአይኖሩም። አብዛኛዎቹ ትላልቅ ልጆች ወላጆቻቸው ባይገኙም ምንም አይሆኑም።

አንስትሲዮሎጂስቱ ልጅዎ የማደንዘዣ መድሐኒት እንዲውድ የሚወሰንም ቢሆንም፣ ከቀዶ ጥገና ሕክምናው ቀን የእርስዎ ወይም የልጅዎ ማንኛውንም ምርጫታሳቢ ይሆናል። አንስትኻያ (የማደንዘዣ መድሐኒት) መውሰድ አደገኛ ሂደት መሆኑን እባክዎን ይገንዘቡ። ሁል ጊዜም ቢሆን የልጅዎን ደህንነት መጠበቅ የአንስትሲዮሎጂስቱ ቀዳሚ ተግባር ነው። ልጅዎ አንስትኻያ በሚወስድበት ጊዜ በቦታው የሚገኙ ከሆነ ልጁ እንቅልፍ እንደወሰደው ወዲያውኑ ወደ ማቆያ ስፍራ ይወሰዳሉ።

## ልጄ ከእንቅልፍ ሲነቃ ለማየት በማገገሚያ ክፍሉ ውስጥ እንድገኝ ይፈቀድልኛል?

ልጅዎ ከእንቅልፍ ሲነቃ እና መረጋጋቱ ሲታወቅ በድህረ አንስትኻያ መንከባከቢያ ክፍል (PACU) ውስጥ አንድ ወላጅ እንዲገኝ ይፈቀዳል።  ልጅዎ ወደ 2ኛው ማገገሚያ ክፍል ሲዛወርና ወደ ቤት ለመሄድ ሲዘጋጅ ሁለቱም ወላጆች መገኘት ይችላሉ። ወንድሞቹና እህቶቹ በማገገሚያ ክፍል ውስጥ እንዲገኙ አይፈቀድላቸውም።

## የሕመም ማስታገሻ መድሐኒት እንዴት ይሰጣል?

የሕመም ማስታገሻ መድሐኒት አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠው በደም ስር ውስጥ ነው። አስፈላጊ ከሆነም ልጅዎ በአፍ የሚወሰድ መድሐኒት ቤቱ እንዲጠቀም ሊሰጠው ይችላል።

# የ SWEDISH MEDICAL CENTER (ስዊድሽ የሕክምና ማዕከል) አንስትሲዮሎጂ ክፍል የታካሚ ስምምነት መግለጫ ቅጽ

አንስትሲዮሎጂ የልዩ ዓይነት መድሐኒት ሳይንስ ነው። የእርሶ አንስትሲዮሎጂስት በሕክምና፣ በቀዶ ጥገና ሕክምና፣ ወይም በኦብስተትሪካል የሕክምና አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት የአንስትዥያ (የሕመም ማደንዘዢያ) ሕክምና አገልግሎት እንዲያደርጉልዎት የሰለጠኑ ሐኪም ናቸው። የአንስትዥያ ሕክምናዎ የስዊድሽ ዲፓርትመንት ኦፍ አንስትሲዮሎጂ አባል በሆኑ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አንስትሲዮሎጂስቶች (ሐኪሞች) ይሰጣል። ይህ የታካሚ የስምምነት መግለጫ ቅጽ ለቀዶ ጥገና ወይም ለሌላ የውስጥ ሰውነት ሕክምና (ለኢንቬሲቭ ፕሮሲጀራል ትሪትመንት) ቅጽ ስምምነት ተጨማሪ ነው።

ተከታዩ መረጃ ጥቅም ላይ ስለሚውለው አንስትዥያ ወይም የእንቅልፍ መድሐኒት መግለጫ እና ሊኖሩ የሚችሉ አደጋዎች ዝርዝር ነው። መረጃው ስለሚሰጠው የአንስቴቲክ (ማደንዘዢያ መድሐኒት) ሕክምና እርሶ ለማወቅ እንደሚያችልዎትና የአንስትሲዮሎጂ ሐኪምዎን (አንስትሲዮሎጂስት) ጥያቄ እንዲጠይቁ እንደሚያደርግዎት ተስፋ ይደረጋል። ይህ ዝርዝር እርሶን ለማስደንገጥ ወይም ለሕክምናዎ ተስፋ እንዲቆርጡ ለማድረግ አይደለም፣ ግን ሁሉም ዓይነት ሕክምናዎች አደጋ ሊኖራቸው እንደሚችሉ እንዲያውቁ ለማድረግና፣ አልፎ አልፎ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች መሆን እንደሚችሉ እርሶ እንዲያውቁ ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ አደጋዎችና ውስብስብ ሁኔታዎች በሚከተሉት ሳይወሰኑ ሊያጠቃልሉ የሚችሉት፥

<u>**አጠቃላይ አንስትዥያ**</u>፥ ማቅለሽለሽ፣ አለርጂ/ከፍተኛ የመድሐኒት መጣላት ሁኔታ፣ ጉሮሮ የመከርከር፣ የጉሮሮ መጎርናት፣ የከንፈሮች/ጥርስ/የድምፅ አውታር/የአየር መተላለፊያ መቁሰል፣ የመበከል (ኢንፌክሽን)፣ ኒሞኒያ (የሳምባ ምች)፣ አስፓይሬሽን (የሰውነት ፈሳሽ የማውጣት)፣ የነርቭ መጎዳት፣ የዓይን መጎዳት፣ የአርተሪ (ደም ቅዳ) ወይም የደም ስሮች መጎዳት፣ አንስትዥያ (ማንደንዘዢያ) ተደርጎ ሳለ አለማነቀላፋት፣ ሰውነት የመጣል ሁኔታ (ሲዠር)፣ ሽባ የመሆን፣ የልብ ምታት፣ የልብ/ሳምባ/አንጎል መቁሰል፣ እና ሞት።

<u>**ኑራክሲያል አንስትዥያ**</u> (ኢፒዱራል ወይም የአከርካሪ)፥ የጀርባ ሕመም፣ ራስ ምታት፣ የደም ግፊት መለወጥ፣ ኢፒዱራል ወይም አከርካሪ በደንብ አለመደንዘዝና አጠቃላይ አንስትዥያ (ማደንዘዢያ) ማስፈለጉ፣ የመድማት፣ መድሐኒት የመጣላት፣ የመተንፈሻ አካል መዳከም፣ የመበከል (ኢንፌክሽን)፣ የነርቭ ጉዳት፣ ሽባ የመሆን፣ ሰውነት የመጣል (ሲዠር)።

<u>**ሪጂናል (ለተወሰነ የሰውነት ክፍል) አንስትዥያ**</u>፥ አነስተኛ ሕመም ወይም አለመመቸት፣ አለርጂ፣ የተወሰነ የሰውነት ክፍል እንዲደነዝዝ ማድረግ አለመቻል፣ መድማት፣ የመበከል (ኢንፌክሽን)፣ የነርቭ ጉዳት፣ የደም ቅዳ (የአርተሪ) ወይም የደም ስር መቁሰል፣ የሰውነት መደንዘዝ ወይም መድከም፣ የመተንፈሻ አካል መዳከም፣ የሰውነት መጣል (ሲዠር)፣ የአከርካሪ ወይም ኢፒዱራል መዘጋት፣ የራስ ምታት፣ የልብ ምታት፣ የልብ/ሳምባ/አንጎል መቁሰል፣ ሞት፣ እና አጠቃላይ አንስትዥያ የማስፈለግ።

<u>**ትራንስኢሶፋጊያል ኢኮካርዲዮግራፊ**</u>፥ የጉሮሮ መቁሰል፣ የከንፈር፣ የጥርስ፣ የአፍ፣ የጎሮሮ፣ የጨጓራ ጫፍ(ኢሶፋገስ)፣ ወይም የጨጓራ መቁሰል፣ የድምፅ መጎርናት፣ መዋጥ አለመቻል፣ ለመዋጥ የሕመም ስሜት መኖር፣ አስፓይሬሽን (የሰውነት ፈሳሽ የማውጣት)፣ እና የመበከል (ኢንፌክሽን)።

ለማንኛውም ቀዶ ጥገና ሕክምና ወይም የሕክምና አገልግሎት አንስትዥያ (ማደንዘዢያ) መውሰድ አደጋ ሊኖረው እንዲሚችልና ለአንስተቲክ (ለማደንዘዢያ መድሐኒት)፣ ለሌሎች መድሐኒቶች ወይም የማደንዘዢያ መድሐኒት ከመውሰድ ጋር ለሚገናኙ የሕክምና አገልግሎቶች ሰውነቴ ሊያሳይ ስለሚችለው ሁኔታ ምንም ዓይነት ቃል ኪዳን ወይም ዋስትና ሊሰጥ እንደማይቻል ይገባኛል። ሁሉም የሕክምና አገልግሎቶች ያልታሰቡ አደጋዎች ሊኖሯቸው ይችላል።

ለተወሰኑ የሕክምና አገልግሎቶች በጣም ጠንከር ያለ ክትትል ሊያስፈልግ እንደሚችል ይገባኛል፣ እንደ የልብ ደም ቅዳ ደም ስር (አርትሪያል ላየንስ)፣ መሃከለኛ መሥመሮች፣ ወይም ትራንስኢሶፈጋል ኢኮካርዲዮግራፊ ለመሰሉት። በሕክምናዬ ወቅት፣ የሰውነት ሁኔታዬ ሊለወጥ ይችላል፣ እናም የአንስትዥያ (ማደንዘዢያ መድሐኒቱ) እና/ወይም የክትትሉ ዓይነት ሊለወጥ ይችል ይሆናል። በእኔ የአንስትዥያ (የማደንዘዢያ) ዕቅድ ላይ የሚኖር ማንኛውም ለውጥ ሐኪሜ (አንስተዚዮሎጂስት) ለደህንነቴ ቅድሚያ በመስጠት የሚያደርጉት ይሆናል።

ለሐኪሜ (ለአንስትሲዮሎጂስት) እና ለሌሎች የጤና ጥበቃ አገልግሎት አቅራቢዎቼ ስለ ሁሉም መድሐኒቶቼ፣ ከሐኪም ስለሚታዘዝልኝ መድሐኒት፣ ያለ ሐኪም ትዛዝ ስለሚገዙ መድሐኒቶች፣ ስለ አማራጭ መድሐኒቶችና ለምግብ ተጨማሪ ቪታሚኖች፣ እና ማንኛውንም ሌላ የመዝናኛ ዕፅ ወይም አልኮሆል ስለመጠቀምም ጨምሮ ማሳወቄን አረጋግጣለሁ። ደግሞም፣ ስላለብኝ የሚታወቁ አለርጂዎች፣ ስለ የሕክምና ታሪኬ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት ስለነበረብኝ ማንኛውም የአነስተቲክስ (ማደንዘዢያ መድሐኒት) ማንኛውም ችግር ለሐኪሜ ማሳወቄን አረጋግጣለሁ። ስዊድሽ ሆስፒታል ትምህርት የማስተማሪያ ተቋም እንደሆነ፣ እና ነዋሪ ሐኪሞች (ሬዚደንት) ወይም ባልደረባዎች (ፌሎ) በሐኪሜ (በአንስትሲዮሎጂስት) እየተመሩ በአንስትዥያ ሕክምናዬ ላይ ተካፋይ እንደሚሆኑ ይገባኛል። ነዋሪ ሐኪምዎቹ (ሬዚደንት) ወይም ባልደረባዎቹ (ፌሎ) በሕክምናዬ ላይ እንዳይካፈሉ ለይቼ ልከለክል እችላለሁ። የ DNR ትዛዜ ተፈጻሚ እንዲሆን ለቀዶ ጥገና ሐኪሜ ወይም ለእኔ አንስትሲዮሎጂስት በግልጽ ካልተናገርኩ በስተቀር፣ ለአንስትዥያው በመስማማቴ፣ አንስትዥያ መደሐኒቱ ከሚያስከትላቸው ሁኔታዎች በጠቅላላ እስከሚሻለኝ ድረስ የማናቸውም "ትንፋሽ እንዲመለስ አታድርግ (ዱኖት ሪሰስቴት)" ትዛዞች ለጊዜው ተፈጻሚ እንዳይሆኑ መስማማቴ እንደሆነ ይገባኛል።

ስለ አንስቴቲክ መድሐኒት (የማደንዘዢያ መድሐኒት) ላሉኝ አማራጮች፣ እንዲሁም ለተለያዩ አማራጮች ሊኖሩ ስለሚችሉት አደጋዎችና ጥቅሞች መረጃ እንደተሰጠኝ ይገባኛል። በዚህ የአንስተቲክ ዕቅድ ላይ፣ ከእኔ ጋር ውይይት በተደረገባቸው የመድሐኒት አሰጣጥና ክትትል ላይም ጨምሮ እስማማለሁ። ለአንስተቲክ መድሐኒት ዕቅድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልሶችና መረጃዎች እስከምረካ ድረስ ጥያቄዎችን ለመጠየቅና ውይይት ለማድረግ እድል እንደነበረኝ ወይም እንደሚኖረኝ ይገባኛል። የአንስቴቲክ መድሐኒቱ መሰጠቱ ከመጀመሩ በፊት በማንኛውም ሰዓት ላይ ይህን ስምምነት ላነሳ እንደምችል ይገባኛል።

የታካሚ ወይም
የታካሚ ተወካይ ፊርማ ______________________________ ቀን ______________ ሰዓት ____________

የታካሚ / ተወካይ ስም በህትመት ፊደል ሲጻፍ ______________________________

የአንስትሲዮሎጂስት ፊርማ ______________________________ ቀን ______________ ሰዓት ____________

የአንስትሲዮሎጂስት ስም በህትመት ፊደል ሲጻፍ ______________________________

PATIENT LABEL

SWEDISH
SEATTLE, WASHINGTON

Form 76248-AMHARIC Nonstock Rev. 9/09 CC

ናሙና

የ SWEDISH MEDICAL CENTER (ስዊድሽ የሕክምና ማዕከል) አንስትሲዮሎጂ ክፍል የታካሚ ስምምነት መግለጫ ቅጽ

# ሆስፒታል ውስጥ ለመቆየት ከመምጣትዎ በፊት ማወቅ የሚገባዎት ነገሮች

### በሆስፒታሉ ውስጥ ሕክምና በሚከታተሉበት ወቅት የሚጎበኙዎት ሰዎች

በ Swedish የሕክምና ማዕከል ታካሚዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ቤተሰብ እና ጓደኞች ሆስፒታል ውስጥ በመታከም ላይ ያለውን ልጅዎን መጎብኘታቸው ለልጁ ጤንነት መሻሻል እንደሚረዳ እናውቃለን። ሆኖም ግን፣ የታካሚውን ደህንነት ለመጠበቅ እና እረፍት እንዲያገኝ ወይም ክፍሉ ውስጥ ሌላ ታካሚ ሊኖር ስለሚችል የሆስፒታሉ ሰራተኛ ታካሚውን የሚጎበኙ ሰዎችን ቁጥር ሊገድቡ ይችላሉ። ታካሚዎን ለመጠየቅ አመቺ ስለሆነው ጊዜ እና ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንደሚቻል ለማወቅ እባክዎን ከነርሷ ጋር ይነጋገሩ። ሁሉም ሰው በተመሳሳይ ጊዜ ለመጎብኘት እንዳይመጣ ቤተሰቦች እና ጓደኞች ታካሚውን የሚጠይቁበትን ጊዜ በቅድሚያ እንዲያቅዱ ይጠየቃሉ።

### ከጉብኝት ሰዓት በኋላ የሚመጡ ጠያቂዎች ካሉ የጉብኝዎች መታወቂያ ባጅ ሊኖራቸው ይገባል።

ከምሽቱ 9 ሰዓት ከሆነ በኋላ ወይም ከጥዋቱ 5 ሰዓት በፊት የሚመጡ ካሉ ለደህንነት ሲባል ጊዜያዊ ባጅ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። የጉብኚ መታወቂያ ባጅ ለማግኘት እንዲረዱዎት እባክዎን በሕክምና ክፍሉ ውስጥ የሚሰሩትን ነርስ ይጠይቋቸው። ከጉብኝት ሰዓት በኋላ ያለ ባጅ ሆስፒታል ውስጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው በደህንነት የጥበቃ አባላት ይጠየቃል።

### የቤት እንስሳት እና አገልግሎት ሰጪ እንስሳት

የቤት እንስሳት የታካሚው ቤተሰብ አባል ተደርገው እንደሚቆጠሩ እናውቃለን። ሆኖም ግን ባጠቃላይ የጤንነት ችግሮች ምክንያት ለጉብኝት ወደ ሆስፒታሉ መምጣት የሚችሉት አገልግሎት ሰጪ እና ለቴራፒ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑት ብቻ ናቸው።

### ሲጋራ የሚያጨሱ ከሆነ

በ Swedish ተልእኳችን የምናገለግላቸውን የእያንዳንዱን ሰው ጤንነትና ደሕንነት ለማሻሻል ነው፣ ታካሚዎችን፣ ቤተሰቦችን፣ ጎብኝዎችን፣ የሕክምና ባልደረቦችን፣ ሐኪሞችን፣ ፈቃደኞችንና ሌሎችን ምጨምሮ። የዚያ ተልኮ አካል የሆነውም ከአደጋ የተጠበቀና ጤናማ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ ነው። ጤናማ አካባቢ ከጭስና ከትምባሆ ነጻ የሆነ ተቋምን ያጠቃልላል። Swedish፣ እኛ በውስጥም ሆነ በውጭ፣ በሁሉም ካምፓሶቻችንና በሁሉም የውጭ መታከሚያ ክሊኒኮቻችን ሁሉ፣ ከጭስና ከትምባሆ-ነጻ ነን ሲል ኩራት ይሰማዋል። ይህ ፖሊሲ፣ የኤሌክትሮኒክ ስጃራዎችን (e-cigarettes) ወይም ሌሎች ተመሳሳይ መሳሪያዎችን፣ እንዲሁም የሚታኘኩ የትምባሆ ምርቶችንንም ያጠቃልላል። ልጅዎ በሆስፒታል ውስጥ በሕክምና ላይ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሲጋራ ለማጨስ የሆስፒታሉን ህንፃ ለቅቆ መውጣት አይፈቀድለትም። ልጅዎ የኒኮቲን ውጤቶች ሱሰኛ ከሆነ፣ ለኒኮቲን መተኪያ ሕክምናዎችን እናቀርባለን፤ ይህ አገልግሎት ዝግጁ ሲሆን በኢንሹራንስ ጥቅሞች ክፍያ ውስጥ ይካተታል።

ሲጋራ ለማጨስ የሚፈልጉ ጎብኝዎች በ Swedish ንብረት ላይ ወይም መኪና ማቆሚያ ጋራጆች ውስጥ መሆን የለባቸውም፣ እናም ከሕንጻ መግቢያዎች፣ መውጫዎች፣ ሊከፈቱ ከሚችሉ መስኮቶች፣ ከአየር ኮንዲሽነሮች፣ ከአየር ማናፈሻዎች ወይም ከሌሎች የአየር ማስገቢያ ዘዴ መሣሪያዎች፣ በሕግ እንደተጠቀሰው ቢያንስ 25 ጫማ የራቁ መሆን አለባቸው።

እርሶ ወይም ማናቸውም ጓደኞችዎ፣ ቤተሰብዎ፣ ወይም ጎብኛችዎ ሲጋራ ማጨስ ለማቆም የሚረዳቸው ፕሮግራምን Swedish ይደግፋል። ስለ ፕሮግራሙ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎን 1-800-QUIT-NOW ይደውሉ።

### የኤሌክትሪክ መሳሪያዎችን መጠቀም።

በሆስፒታሉ ውስጥ የእጅ ስልክ፣ ፔጀር ወይም ላፕቶፕ ኮምፒውተር መጠቀም የሚቻለው በገደብ ነው። ከማንኛውም የሕክምና መሳሪያ ቢያንስ 10 ጫማ ያህል መራቅ አለብዎት። እነዚህን መሳሪያዎች ለመጠቀም ኮሪደሮችና ማረፊያ ክፍሎች የተሻሉ ቦታዎች ናቸው።

### መውደቅን ማስወገድ

ሆስፒታል የሚቆዩበት ጊዜ የመውደቅ አደጋ ሊደርስብዎት ይችላል። እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሊፈጠር የሚችለው ታካሚው አካባቢውን በደምብ ሊለማመደው ባለመቻሉ፣ በመድሐኒቶች ምክንያት፣ በተቀያየረ የእንቅልፍ ሰዓት ወይም እንቅስቃሴን አስቸጋሪ በሚያደርጉ ቱቦዎች፣ አውታሮች ማሽኖች ምክንያት ሊሆን ይችላል። መውደቅ በልጅዎ የማገገሚያ ሁኔታ ላይ አዲስ ቁስል ወይም ችግር ሊያመጣ ስለሚችል እነዚህን አደጋዎች ለመከላከል የሚቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች በመከተል ሊረዱ ይችላሉ፦

- ልጁ አልጋ ውስጥ ሲገባ እና ከአልጋው ሲወጣ ያግዙት
- ልጅዎ ቀስ ብሎ እንዲነሳ ያድርጉት
- ልጅዎ የማያንሸራትት ጫማ እንዲያደርግ ያስጠንቅቁት
- የፈሰሰ ማንኛውን ነገር ካለ ያሳውቁ
- የምሽት-መብራት ይጠቀሙ
- ልጅዎ በመታጠቢያ ቤት ውስጥ እና በአዳራሽ ውስጥ የእጅ መደገፊያ እንዲጠቀም ይምከሩ
- ከተቻለ፣ ልጅዎ እንደ ዋከርና ከዘራ የመሰሉትን የሆስፒታሎን እቃዎች እንዲጠቀም ያድርጉ

## የመገናኛ ኢጋዥ መሣሪያዎች

ስዊድሽ በታካሚው ጥያቄ መሠረት፣ የአስተርጓሚ አገልግሎት፣ የምልክት ቋንቋ መተርጐሚያ፣ ድጋፍ ሰጪ መሣሪዎችን፣ በጽሁፍ የተተረጎሙና ትላልቅ-ለታካሚ የታተሙ ጽሁፎችን ያለምንም ክፍያ በነፃ ሊያቀርብ ይችላል። እርስዎ፣ ልጅዎ፣ ጠያቂዎችዎ ወይም የሚያግዝዎት ሰው የማየት የመናገር እና/ወይም የመስማት ችሎታቸው የቀነሰ ከሆነ ወይም እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋዎ ካልሆነ እና በቋንቋ ለመግባባት ድጋፍ ካስፈለገዎ፣ እባክዎን ይንገሩን።

## ወደ ቤት ለሚወሰዱ መድሐኒቶች ክፍያ መክፈል

ልጅዎ ከስዊድሽ ሆስፒታል ሲወጣ፣ ልጅዎ እቤት ወሰዶ እንዲጠቀም ዶክተር አንድ ወይም ከዚያ በላይ መድሐኒት ሊያዝ ይችላል። ከዚህ በታች የተሰጠው መረጃ ለእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ቀድመው እንዲያቅዱ ይረዳዎታል፥

- ከሆስፒታል ሲወጣ/ እቤት ለሚወሰድ መድሐኒት(ቶች) ወጪ፡እንዲከፍሉ ጥሬ ገንዘብ ወይም ዴቢት ወይም ክሬዲት ካርድ ይዘው ይምጡ።
- ከግቢያችን (Cherry Hill፣ Edmonds፣ First Hill፣ Issaquah ወይም የ Orthopedic Institute) ውስጥ ካሉት በአንዱ የስዊድሽ ፋርማሲ ወይም ውጪ ካለ ፋርማሲ ልጅዎ ከሆስፒታል ሲወጣ የሚታዘዙለትን መድሐኒቶች ለማስሞላት ሊመርጡ ይችላሉ።
- ወደ ፋርማሲ ይዘው እንዲሄዱ ለልጅዎ መድሐኒት የታዘዘበትና የተፈረመበትን ወርቀት ኮፒ እንዲሰጡዎት ዶክተሩን ወይም ነርሷን ይጠይቁ። በመረጡት በማንኛውም ፋርማሲ ሲሄዱ የወረቀቱ ኮፒ ሁልጊዜም ቢሆን ያስፈልጋል።
- የታዘዘውን የልጅዎን መድሐኒት ሊወሰዱ ሲሄዱ እባክዎን ክፍያውን ለመክፈል ይዘጋጁ። የሚከፍሉት ክፍያ የሚወሰነው ለልጆዎ በታዘዘው መድሐኒት ኢንሹራንስ ይወሰናል (የግል ኢንሹራንስ፣ ሜዲኬር ሜዲኬድ እንዲሁም የሌበር እንድ ኢንዱስትሪ ክፍያዎችን ጨምሮ)። ልጅዎ ለሚታዘዝ መድሐኒት ኢንሹራንስ ካለው፣ እባክዎን ትክክለኛ የሂሳብ መረጃ መያዛችንን እርግጠኛ እንድንሆን መድሐኒቱን በሚወስዱብት ግዜ የመድሐኒት ትዕዛዝ ኢንሹራንስ ካርድ ይያዙ።

# 10 የጥንቃቄ ጤና ጥበቃ ጥቆሚ ሃሳቦች

## ስለ እርሶ ጤና ጥበቃ ቋሚ አጋር ለመሆን ምን ማድረግ አለቦት።

*ጥሩ የጤና ጥበቃ ሊያገኙ የሚችሉት በእርሶ እና በጤና ጥበቃ አቅራቢዎች መሃከል በሚኖረው ሽርክነት መሰረት ነው። ጥሩ የጤና ጥበቃ አገልግሎት እንዲያገኙ ከሐኪምዎ ጋር እንዴት መስራት እንደሚችሉ ከዚህ በታች ጥቂት ጥቆማዎች ይገኛሉ።*

### 1. ለጤና እንክብካቤዎ ተሳትፎ ያድርጉ።

- ለእያንዳንዱ ሐኪም ምን ዓይነት የጤና እንክብካቤ እንደነበረዎትና ማን እንዳከመዎት ይናገሩ።
- በዶክተሩ ያልታዘዙ ሌሎች ሕክምናዎች ማድረግዎን ይንገሯቸው፣ ለምሳሌ በዕፅዋት ሕክምና፣ እቤት የሚሰጡ መድሐኒቶች ወይም አኩፓንቸር ተጠቅመው እንደሆነ ይግለፁላቸው።
- ለሐኪምዎ ሊያስፈልግዎ ስለሚችሉ ባህላዊና መንፈሳዊ እርዳታዎች ይንገሯቸው።
- የጤንነት መመሪያዎችን መረዳትዎን ለማረጋገጥ ለቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ደጋግመው ይንገሩ።
- ስለሚደረግልዎት ማንኛውም ዓይንት ሕክምና ያልገባዎት ነገር ካለ ማንኛውም ሐኪም እንዲያውቀው ያድርጉ። አንድ ነገር ለደህንነትዎ ጥሩ የሚይሆን ከመሰለዎ ወዲያውኑ ለሐኪሞችዎ ይንገሯቸው።

### 2. ይጠይቁ፣ ይጠይቁ፣ ይጠይቁ።

- የሕክምና አገልግሎት አቅራቢ ሲመርጡ ስለ ሕክምናዎ በቀላሉ ሊያናግሩት የሚችል ሐኪም ይምረጡ።
- መቼ እና እንዴት ማንኛውንም የምርመራ ወይም የሕክምና ውጤቶች እንደሚያገኙ ሐኪምዎን ይጠየቁ። ውጤቶቹን ሲያገኙ፣ ምን እንደሚሉ ማወቅዎን ያረጋግጡ።
- ስለ ሕክምናው አማራጮች፣ ስለሚያስከትለው አደጋ እና ሕክምናው እንዴት ሊረዳ እንደሚችል ሐኪምዎ እንዲያስረዱዎት ያድርጉ።
- የትኛውን ሕክምና እንደሚመርጡ እርግጠኛ ካልሆኑ ሁለተኛ አስተያየት ከሌላ ሰው ያግኙ።
- እንዲሻልዎ ምን ዓይነት ለውጥ ማድረግ እንዳለብዎት ይወቁ።

#### ተጨማሪ መረጃዎች፥

- እነዚህን የቅድሚያ መመሪያዎች በመሙላት ስለሕክምናዎ በቅድሚያ ውሳኔ ይስጡ፥
  - መወሰን በማይችሉ ጊዜ እርሶን ወክሎ የሚናገርልዎት ሰው ለመምረጥ የተወካይ (ፓወር ኦፍ አቶርኒ) ቅጽ።
  - በህይወት እንዲቆዩ መቼ ወይም እንዴት ሕክምና እንደሚታከሙ ለሐኪምዎ የሚገልጽ የሕክምና መመሪያ ቅጽ፣ ወይም ኑዛዜ።
- ስለ ቅድሚያ መመሪዎች የበለጠ ለማወቅ ይጠይቁ፥
  - የእርስዎ ሐኪም
  - በቅድመ መግቢያ የክሊኒክ ቀጠሮ ወቅት የእርሶ ነርስ

### 3. በሕክምናው ወቅት የእርስዎ አጋር እንዲሆን የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ይዘው ይምጡ።

- እርስዎን ወክሎ የሚናገር እና የሚረዳዎት ሰው ይምረጡ።
- ቤትዎ ውስጥ ያለው የእርስዎን የሕክምና መዝገብ የት እንዲሚያገኙ ለአጋርዎ ያሳዩ። ምን ዓይነት መድሐኒት እንደሚወስዱ እና የት እንዳለ ይንገሩዋቸው።
- በምርመራዎ፣ በሕክምናዎ እና ሆስፒታል በሚሆኑበት ወቅት አጋርዎ ከርስዎ ጋር እንዲቆዩ አቅድ ያውጡ።
- የሕክምና አጋርዎ ጥያቄ ቢጠይቁና በማስታወሻ ቢጽፉም ምንም አይደለም።

### 4. የሚያክምዎት ሐኪም እርስዎን ከማከሙ በፊት ስለእርስዎ ማወቅ ይኖርበታል።

- ሐኪሞች እርሶን ከማከማቸው በፊት በእያንዳንዱ ጊዜ ላይ ሁለት ዓይነት መታወቂያዎችን እንዲመርመሩ ይጠይቋቸው።
- በእጅ ላይ የሚታሰር መለያ ከተሰጠዎት ስምዎ እንዳለበት እና የስምዎ ፊደል በትክክል እንደተጻፈ ያረጋግጡ።
- በተጨማሪም፣ በሚሙዎት የጤና ባለሞያዎች ባጅ ላይ ስማቸውን ይመልከቱ።

### 5. የሚወስዱትን መድሐኒቶች ዝርዝር በሙሉ ለሐኪም ያሳዩ።

- በዝርዝሩ ላይ የመድሐኒቶችን፣ የቫይታሚኖችን፣ የዕጽዋቶችን እና የምግብ መጨመሪያ ማዕድኖችን ሁሉ ይጻፉ።
- ሐኪም በሚጎበኙበት በእያንዳንዱ ግዜ ላይ ዝርዝሩን ያምጡ።
- ስላሉብዎ አላርጂ ሐኪምዎ እንዲውቁት ያድርጉ።
- መድሐኒቶች በእርስዎ ላይ ያደረሱት ጉዳት ካለ ለሐኪምዎ ያሳውቋቸው።

## 6. ስለ መድሐኒቶችዎ በደንብ ይወቁ።

- አዲስ መድሐኒት የሚወሰደው ለምን እነደሆነ እና እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል ሐኪሙን ይጠየቁ።
- የታዘዘልዎን መድሐኒት የንግድ ምልክት ስም እና ሌላ ማንኛውም ዓይነት ስም ይወቁ።
- መድሐኒቱን እንዴት እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚወስዱት ይወቁ።
- መድሐኒቱን ሲወስዱ ለምን ነገር መጠንቀቅ እንዳለብዎት ባለ ፋርማሲው የጽሁፍ መረጃ እንዲሰጥዎት ይጠይቁ።

## 7. በበሽታ መመረዝን (ኢንፌክሽን) ይከላከሉ።

- እጅ የሚያጸዳ አልኮል ይጠቀሙ ወይም እጅዎን ይታጠቡ። እንዳይታመሙ የእጅ ንጽህናን መጠበቅ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው።
- እርስዎን የሚንከባከቡ ማንኛውንም ሰው፣ "የእጅ ንጽህና መጠበቂያ አልኮል ተጠቅመዋል ወይም እጅዎን ታጥበዋል?" ብለው ይጠይቋቸው።
- ቤተሰብዎ እና ጓደኞችዎ፣ ጉንፋን፣ ፍሉ ወይም ሳል ከያዛቸው እንዳይጎበኝዎት ወይም ከርስዎ ጋር እንዳይሆኑ ይንገሩዋቸው።

## 8. ለሕክምናው እና ለቀዶ ጥገናው ይዘጋጁ።

- ከሕክምናው ወይም ከቀዶ ጥገናው በፊት ምን መድሐኒት መውሰድ ወይም አለመውሰድ እንዳለብዎት፤ ምን መብላት ወይም መጠጣት እንደሚችሉ ወይም እንደማይችሉ፣ እና ምን መልበስ እንዳለብዎት ወይም እንደሌለብዎት ማወቅ ይገባዎታል።
- በሕክምናው ወይም በቀዶ ጥገናው ወቅት ምን መደረግ እንዳለበዎት እርስዎ እና ሐኪሞችዎ ሁሉ መስማማት መቻላችሁን አረጋግጡ።
- ሐኪሞችዎ ቀዶ ጥገና የሚደረግበትን የሰውነት ክፍልዎን ቦታ እንዲያገኙት እና ምልክት እንዲያርጉበት ይርዷቸው።
- ቀዶ ጥገና የሚደረግበት የሰውነት ክፍል ላይ ብቻ ምልክት መደረጉን ያረጋግጡ። በሌላ ቦታ ላይ ምልክት ከተደረገ ሊያደናግር ይችላል።

## 9. እቤትዎ ሲሆኑ ራስዎን ለመንከባከብ ምን ማድረግ እንዳለብዎት እንዲገልጽልዎት ሐኪሞችዎን ይጠይቁ።

- የተለመደውን ተግባርን እንደገና መጀመር የሚችሉት መቼ እንደሆነ ይወቁ።
- ጥያቄ ሲኖርዎት የሚጠየቁትን ሰው የስልክ ቁጥር ያግኙ።
- የሚቀጥለው ቀጠሮ መቼ እና የት እንደሚሆን ይወቁ።
- መመሪያዎቹን የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ እንዲያዳምጥ ያድርጉ።

## 10. ስለ ጤና እንክብካቤዎ እና ሕክምናዎ ይወቁ።

- ስለ ጤናዎ እንክብካቤ እና ሕክምና በተቻለ መጠን ብዙ መረጃ ለማግኘት ይሞክሩ።
- የኦንላይን የጤና ቤተ መጻሕፍታችንን በ www.swedish.org/healthlibrary ይጎብኙ። የኦንላይን ቤተ መጻሕፍቱ የብዙ መረጃ ምንጭ ሲሆን፣ ስለ ሕክምና እና ቀዶ ጥገና እውነታ ጽሁፎች እንዲሁም ብዙ የጤና ሁኔታዎች፣ መድሐኒቶች፣ እና ሕክምና አማራጮች መረጃዎችን ይዟል።

**መጠየቅ ይቻላል**

ስለማንኛውም ዓይነት የጤና እንክብካቤዎ ለመጤቅ ከፈለጉ መጠየቅ ይቻላል።

# FAQ

(ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች)

## “የቀዶ ጥገና የሚደረግባቸው ቦታዎች ላይ ስለሚኖር ቁስል ማመርቀዝ”

### *ሰርጂካል ሳይት ኢንፌክሽን (SSI) ማለት ምን ማለት ነው?*

ሰርጂካል ሳይት ኢንፌክሽን ማለት የቀዶ ጥገናው በተካሄደበት ቦታ ላይ ከቀዶ ጥገናው በኋላ የሚከሰት የቁስል ማመርቀዝ ነው። የቀዶ ጥገና የሚደረግላቸው አብዛኛዎቹ በሽተኞች የቁስል ማመርቀዝ (ኢንፌክሽን) አይኖርባቸውም። ሆኖም ግን የቀዶ ጥገና ከሚደረግላቸው 100 ሕመምተኞች መካከል ከ 1 እስከ 3 ገደማ የሚሆኑት የቁስል ማመርቀዝ ይኖርባቸዋል።

ከቀዶ ጥገና ቦታ ላይ ከሚታዩት የቁስል ማመርቀዝ መካከል የተለመዱት ጥቂቶቹ ምልክቶች፥

- የቀዶ ጥገና ከተደረገበት የሰውነት አካል አካባቢ መቅላት እና የሕመም ስሜት
- ቀዶ ጥገና ከተደረገበት አካል ጉም የሚመስል ፈሳሽ ይወጣል
- ትኩሳት

### *SSI ለማከም ይቻላል?*

አዎ። አብዛኛዎቹን የሰርጂካል ሳይት የቁስል ማመርቀዝ በአንቲ ባዮቲክስ ማከም ይቻላል። ለእርስዎ የሚሰጥዎት አንተባዮቲክ የሚወስነው ለቁስል ማመርቀዙ ምክንያት በሆነው ባክቴሪያ (ጀርም) ይወሰናል። አንዳንድ ጊዜ የ SSI ተጠቂ በሽተኞች የቁስል ማመርቀዙን ለመታከም ሲባል ሌላ ቀዶ ጥገና ያስፈልጋቸዋል።

### *SSIን ለመከላከል ሆስፒታሎች የሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?*

SSIን ለመካለከል፣ ዶክተሮች፣ ነርሶች እና ሌሎች የጤና ተንከባካቢዎች፥

- ከቀዶ ጥገናው በፊት ጀርሞችን ለመከላከል እጃቸውንና ክንዳቸውን እስከ ክርናቸው ድረስ በአንቲ ሴፕቲክ መድሐኒት ያፀዱታል።
- እያንዳንዱን ታካሚ ከማከማቸው በፊት እና በኋላ የሕክምና ባለሙያዎቹ እጆቻቸውን በውሃ እና በሳሙና ወይም በአልኮል የእጅ መጥረጊያ ያጸዳሉ።
- ሕክምናው በሚደረግበት አካል አካባቢ ፀጉር ካለ የቀዶ ጥገናው ከመካሄዱ በፊት ወዲያውኑ የተወሰነውን ፀጉርዎን በኤሌክትሪክ ክሊፐር ሊላጩት ይችላሉ። የሕክምና ባለሙያዎቹ ፀጉሩን በምላጭ መላጨት የለባቸውም።
- የቀዶ ጥገና የሚደረግበትን አካባቢ ጽዱ ለማድረግ የቀዶ ጥገናው በሚካሄድበት ወቅት የሕክምና ባለሙያው የተለየ የፀጉር መሸፈኛ ማድረግ፣ የፊት መሸፈኛ፣ ጋውንና የእጅ ጓንት ያደርጋሉ።
- የቀዶ ጥገናውን ከመጀመርዎ በፊት አንቲባዮቲክ ይሰጡዎታል። አብዛኛውን ጊዜ ከቀዶ ጥገናው በፊት በ 60 ደቂቃ ውስጥ አንቲባዮቲክ ማግኘት አለብዎት እንዲሁም ከቀዶ ጥገናው በኋላ በ 24 ሰዓት ውስጥ አንቲባዮቲክ መውሰዱ ሊቆም ይገባል።
- በቀዶ ጥገናው ቦታ ላይ ጀርሞችን በሚገድል በልዩ ሳሙና ቆዳውን ያጸዳሉ።

### *SSIን ለመከላከል እንዲረዳ ምን ማድረግ አለብኝ?*

***ከቀዶ ጥገናው በፊት፥***

- ለሐኪምዎ ሊኖሩብዎት ስለሚችሉ ሌሎች የጤና ችግሮች ይንገሩ። የጤና ችግሮች፣ ለምሳሌ እንደ አላርጂ፣ የስኳር በሽታ እና ውፍረት የመሳሰሉት እክሎች ቀዶ ጥገናውንና ሕክምናውን ሊያስተጓጉሉ ይችላሉ።
- ሲጋራ ማጤስ ያቁሙ። የሚያጨሱ ታካሚዎች የበለጠ ለቁስል ማመርቀዝ ይጋለጣሉ። ከቀዶ ጥገናው በፊት ሲጋራ እንዴት እንደሚያቆሙ ከዶክተሩ ጋር ተነጋገሩ።
- ቀዶ ጥገና በሚደረጉበት አካባቢ አይላጩ። በምላጭ መላጨት ቆዳዎን ሊያስቆጣና ለቁስል ማመርቀዝም ቀላል ሊያደርግ ይችላል።

***ቀዶ ጥገና በሚደርግበት ጊዜ፥***

- ከቀዶ ጥገናው በፊት አንድ ሰው በምላጭሊላጭዎት ከሞከሩ መናገር አለብዎት። የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ለምን መላጨት እንዳለብዎት ይጠይቁ፣ ከዶክተሩም ጋር ተነጋገሩ።
- ከቀዶ ጥገናው በፊት አንቲባዮቲክ ይሰጥዎት እንደሆነ ይጠይቁ።

***ከቀዶ ጥገናው በኋላ፥***

- ሐኪምዎ ለእርሶ የሕክምና ምርመራ ከማድረጋቸው በፊት እጃቸውን በውሃና በሳሙና ወይም በአልኮል ማጽዳታቸውን ያረጋግጡ።

**ሐኪሞችዎ እጃቸውን ሲያጸዱ ካላዩ፣ እንዲያጸዱ ይንገሯቸው።**

- እርስዎን የሚጠይቁዎት ቤተሰቦች እና ጓደኞች የቀዶ ጥገና ቁስሉን ወይም ፋሻውን መንካት የለባቸውም።
- ቤተሰቦችዎና ጓደኞችዎ እርሶን ከመጎብኘታቸው በፊትና በኋላ እጃቸውን በውሃና ሳሙና ወይም በአልኮል ሊያፀዱ ይገባል። እጃቸውን ሲያጸዱት ካላዩ፣ እንዲያፀዱት ይንገሩዋቸው።

### *ከሆስፒታል ወደ ቤቴ ስሄድ ምን ማድረግ አለብኝ?*

- ወደ ቤትዎ ከመሄድዎ በፊት የእርስዎ ዶክተር ወይም ነርስ ቁስልዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ማወቅ ያለብዎትን ነገር ሁሉ ማስረዳት ያስፈልጋቸዋል። ሆስፒታሉን ከመልቀቅዎ በፊት ቁስልዎን እንዴት እንዲንከባከቡት በደንብ መረዳትዎን ያረጋግጡ።
- ቁስልዎን ከማከምዎ በፊትና በኋላ ሁልጊዜም ቢሆን እጅዎን ይታጠቡ።
- ወደ ቤትዎ ከመሄድዎ በፊት፣ ጥያቄ ካለዎት ወይም ችግር ከተፈጠረ ከማን ጋር መገናኘት እንዳለብዎት ማወቅዎን ያረጋግጡ።
- ምንም ዓይነት የቁስል ማመርቀዝ (ኢንፌክሽን) ምልክቶች ካሎት፣ የቀዶ ጥገና ባደረጉበት ቦታ ላይ እንደ መቅላት እና ህመም፣ ፈሳሽ መውጣት፣ ወይም ትኩሳት የሚሳሰሉት ካሉ ለዶክተርዎ ወዲያውኑ ይደውሉ።

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ዶክተርዎን ወይም ነርስዎን ይጠይቁ።

በተባባሪ-ኃላፊነት ያዘጋጁት፥

SHEA The Society for Healthcare Epidemiology of America · IDSA Infectious Diseases Society of America · American Hospital Association · APIC Spreading knowledge. Preventing infection. · CDC Centers for Disease Control and Prevention · The Joint Commission

397273-AMHARIC (12/13)

## ማስታወሻዎች

## ማስታወሻዎች

# አቅጣጫዎች እና የመኪና ማቆሚያዎች

## Cherry Hill

500 17th Ave.
Seattle, WA 98122

**ከደቡብ፥** የ I-5 ሰሜን አቅጣጫ ይዘው ወደ James Street Exit (መውጫ) (164) ይጓዙ። James Street ላይ ወደ ቀኝ (ምስራቅ) ይታጠፉ። James ወደ Cherry Street ይለወጣል። 18th Avenue ላይ ወደ ቀኝ (ደቡብ) ይታጠፉ። Jefferson ላይ ወደ ቀኝ (ምዕራብ) ይታጠፉ። ለዋናው መግቢያ ወደ ቀኝ ይታጠፉ (ሰሜን)።

**ከሰሜን፥** የ I-5 ደቡብ አቅጣጫ ይዘው ወደ James Street Exit (መውጫ) (165A) ይጓዙ። James Street ላይ ወደ ግራ (ምስራቅ) ይታጠፉ። James ወደ Cherry Street ይለወጣል። 18th Avenue ላይ ወደ ቀኝ (ደቡብ) ይታጠፉ። Jefferson ላይ ወደ ቀኝ (ምዕራብ) ይታጠፉ። ለዋናው መግቢያ ወደ ቀኝ ይታጠፉ (ሰሜን)።

### መኪና ማቆሚያ

የአጭር -ጊዜ መኪና ማቆሚያ በአደባባይ ማቆሚያ ቦታ ላይ ይገኛል። በዋናው የመኪና መግቢያ ይግቡ። የረጅም-ጊዜ መኪና ማቆሚያ በ 16th Avenue መኪና ማቆሚያ ውስጥ 16th Avenue ላይ ይገኛል። ከሆስፒታሉ ዋና መግቢያ ሲመጡ፣ Jefferson ላይ ወደ ቀኝ (ምዕራብ) ይታጠፉ። 16th ላይ ወደ ቀኝ (ሰሜን) ይታጠፉ። የመኪና ማቆሚያ መግቢያው አንድ ብሎክ አልፍ ብሎ በስተግራ በኩል ይገኛል። የቫሌ መኪና ማቆሚያ በዋናው መግቢያ ላይ ይገኛል።

### ቅድመ መግቢያ እና የቀዶ ጥገና

የቅድመ መግቢያ እና የቀዶ ጥገና ምዝገባ በዋናው ሎቢ መመዝገቢያ ዴስክ ይገኛል።

## First Hill

**ዋና ሆስፒታል**
747 Broadway
Seattle, WA 98122

**ኦርቶፔዲክ ኢንስቲትዩት (Orthopedic Institute)**
601 Broadway
Seattle, WA 98122

**ከሰሜን፥** የ I-5 ደቡብ አቅጣጫ ይዘው ወደ James Street Exit (መውጫ) (No. 165A) ይጓዙ። James ላይ ወደ ግራ (ምሥራቅ) ይታጠፉ።
**ከደቡብ፥** የ I-5 ሰሜን አቅጣጫ ይዘው ወደ James Street Exit (መውጫ) (No. 164A) ይጓዙ። James ላይ ወደ ቀኝ (ምሥራቅ) ይታጠፉ።
ወደ James እና Broadway መገናኛ ለስድስት ብሎክ ይጓዙ። Broadway ላይ ወደ ግራ (ሰሜን) ይታጠፉ። ወደ ዋናው ሆስፒታል መግቢያ በ Broadway ላይ 1.5 ብሎክ ወደ ግራ ሲታጠፉ ይገኛል። ወደ ስዊድሽ ኦርቶፔዲክ ኢንስቲትዩት የሚወስደው መግቢያ ያለው Cherry Street ላይ አንድ ብሎክ በስተግራ በኩል ነው።

### መኪና ማቆሚያ


ለዋናው ሆስፒታል የፊት መግቢያ፣ ወደ ክቡ የመኪና መግቢያ ለመሄድ ወደ ግራ ይታጠፉ እና ወደ ጋራጅ ለመግባት ምልክቶችን ይከተሉ። ለኦርቶፔዲክ ኢንስቲትዩት፣ Cherry Street ላይ ወደ ግራ ይታጠፉ፣ የጋራጅ መግቢያው በግራ በኩል ነው።

### ቅድመ መግቢያ

ለቅድመ መግቢያ (ዋናውና ኦርቶፔዲክ ክፍል) በዋናው ሆስፒታል አንደኛ ፎቅ ሎቢ ውስጥ የምዝገባ ዴስክ ላይ ይገኛል።

### ቀዶ ጥገና


በዋናው ሆስፒታል የቀዶ ጥገና ምዝገባ የሚገኘው ከአንደኛው ፎቅ ሎቢ አለፍ ብሎ ባለው የምዝገባ ዴስክ ላይ ነው። በኦርቶፔዲክ ኢንስቲትዩት የቀዶ ጥገናው ምዝገባ የሚገኘው በኦርቶፔዲክ እንስቲትዩት ሁለተኛው ፎቅ ላይ ነው።







CHERRY HILL ካምፓስ




FIRST HILL ካምፓስ

## Ballard

5300 Tallman Ave. NW
Seattle፣ WA 98107

**ከሰሜን፥** የ I-5 ደቡብ አቅጣጫ ይዘው ወደ 85th Street Exit (መውጫ) (ቁጥር 172) ይጓዙ። 85th ላይ ወደ ቀኝ (ምዕራብ) ይታጠፉ። ወደ 85th እና 15th Avenue NW መገናኛ ለ30 ብሎክ ይጓዙ። 15th Avenue NW ላይ ወደ ግራ (ደቡብ) ይታጠፉ። ወደ 15th እና Market Street መገናኛ 16 ብሎክ ይጓዙ። Market ላይ ወደ ቀኝ (ምዕራብ) ይታጠፉ። ሶስት ብሎክ ይጓዙና Tall Man Avenue NW ላይ ወደ ግራ (ደቡብ) ይታጠፉ። ወደ መኪና ማቆሚያ ጋራጅ መግቢያ ውስጥ ወደ ቀኝ ይታጠፉ።
**ከደቡብ፥** የ I-5 ሰሜን አቅጣጫ ይዘው ወደ 45th Street Exit (መውጫ) (ቁጥር 169) ይጓዙ። 45th Street ላይ ወደ ግራ (ምዕራብ) ይታጠፉ። ማሳሰቢያ፥ 45th Street ወደ 46th Street ይለወጥና ከዚያም ወደ Market Street ይለወጣል። በ Market ላይ ወደ ምዕራብ ለ 17 ብሎክ ወደ Market እና 15th Avenue NW መገናኛ ይጓዙ። 15th ጎዳናን ያቋርጡ ለሶስት ብሎክ ይጓዙና Tall Man Avenue NW ላይ ወደ ግራ (ደቡብ) ይታጠፉ። ወደ መኪና ማቆሚያ ጋራጅ መግቢያ ውስጥ ወደ ቀኝ ይታጠፉ።

### ቅድመ መግቢያ እና ቀዶ ጥገና

የቅድመ መግቢያ እና የቀዶ ጥገና ምዝገባ በደቡብ ክንፍ በኩል በሆስፒታሉ ሶስተኛ ፎቅ ላይ ነው።

## Issaquah

751 NE Blakely Drive
Issaquah, WA 98029

**ከምስራቅ ወደ ምዕራብ፥** በ 1-90 ላይ ወደ ምስራቅ ወይም ምዕራብ ሲጓዙ፣ ለ E Sunset Way/Highlands Drive ወደ Exit (መውጫ) 18 ይጓዙ።

- ***ወደ ምስራቅ የሚጉዙ ከሆነ፣*** መገንጠያ መንገዱ ላይ በስተግራ በኩል ሆነው ወደ Highlands Drive NE ይቀላቀሉ።
- ***ወደ ምዕራብ የሚጓዙ ከሆነ፣*** Highlands Drive NE/E. Sunset Way ላይ ወደ ቀኝ (ሰሜን) ይታጠፉ፣ በ Highlands Drive NE ላይ መጓዝዎን ይቀጥሉ።

NE Discovery Drive (492 ጫማ) ላይ መጀመሪያው የትራፊክ መብራት ሲደርሱ ወደ ግራ (ምዕራብ) ይታጠፉ። በሚቀጥለው የትራፊክ መብራት ሲደርሱ፣ Eighth Avenue NE (0.2 ማይል) ላይ ወደ ግራ (ደቡብ) ይታጠፉ። መንገዱ ወደ Swedish Issaquah ዋና መግቢያ እስከሚታጠፍ ድረስ በ Eighth Avenue ላይ ቁልቁል ይጓዙ። ከፎቅ ሥር ወዳለው የመኪና ማቆሚያ ለመግባት ወዲያውኑ ወደ ቀኝ ይታጠፉ። ከውጭ ሚዳ ላይም መኪና ማቆሚያ አለ።


### ቅድመ መግቢያ

ለቅድመ መግቢያ መመዝገቢያ 3ኛ ፎቅ ላይ ይገኛል።


### ቀዶ ጥገና

የቀዶ ጥገና ሕክምና መመዝገቢያ አንደኛ ፎቅ ላይ ነው።




BALLARD ካምፓስ




ISSAQUAH ካምፓስ

SWEDISH
PEDIATRICS

www.swedish.org

© 2015 SWEDISH HEALTH SERVICES. ሁሉም መብት የተጠበቀ ነው።